# ይፍጠኑ! ነፃ የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስልጠና ዕድል ይሀውለዎ!

## የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስልጠና በነፃ ስለማግኘት መብት

በኖርዌይ የመኖሪያ ፈቃድዎ በጠቅላላ ለ600ሰዓትታት ያህል ማለትም፥
♦የኖርዌጅኛ ቋንቋን 550ሰዓታት እና
♦የህብረተሰብ ትምህርትን 50ሰዓታት ለመከታተል መብት ይሰጠዎታል።

ስልጠናው በነፃ በሶስት ዓመታት ውስጥ የሚሰጥ ሆኖ ተግባራዊ የሚሆነው፥
♦የመኖሪያ ፈቃድ ካገኙበት ቀን ጀምሮ ወይም
♦ወደኖርዌይ ህጋዊ ፈቃድ ይዘው ከገቡበት ቀን አንስቶ ሊሆን ይችላል።

ማስገንዘቢያ፥ እላይ በተጠቀሱት ሶስት ዓመታት ስልጠናውን ካልጀመሩ ወይም ካላጠናቀቁ ስልጠናውን ከፍለው እንዲማሩ ይደረጋል።

## የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስለመከታተል ግዴታ

የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስልጠናውን በ 600ሰዓታት የማጠናቀቅ ግዴታ የሚያስፈልገው፥
♦ቀዋሚ የነዋሪነት ፈቃድ እና/ወይም
♦የዜግነት መብት ለማገግኘት ማመልከቻ ለማቅረብ ይሆናል።

ይህን ግዴታ በስልጠና ምዝገባ ወቅት ዕድሜዎ 55ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ ግን ተፈፃሚነት አይኖረውም።

ከስልጠናው ግዴታ ነፃ ለመሆን ማመልከት የሚችሉት፥
♦የኖርዌጅኛ ወይም የሳሚኛ ቋንቋ በቂ ችሎታ ያለዎት መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ፥
♦በተለይ የጤና እክል ወይም ሌላ አሳማኝ ምክንያት ካለዎት ይሆናል።

## ተጨባጭ መረጃ

ስልጠናውን ለመውሰድ ወይም ላለመውሰድ መረጃ ከፈለጉ ከተመዘገቡበት የህዝብ ምዝገባ ፅህፈት ቤት አቅራቢያ በሚገኘው የማዘጋጃ ቤቱ የመሰልጠኛ ማእከል በአካል ቀርበው ማመልከት ይችላሉ። የምዝገባ ቀን ማጠናቀቂያ ወይም መብትዎን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት እና መረጃ ከፈለጉ ከማሰልጠኛ ማእከሉ ጋር መገናኘት ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ ከ www.imdi.no እና www.udi.no ማግኘት ይችላሉ።